የዉዝፍ መዛግብት ሰበር ችሎት

ዳኞች:- ሱልጣን አባተማም

ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

ዓለማየሁ ሹናራ

ዘዉዲቱ ታደሰ

የሰበር አመልካች፡- ወ/ሮ ልኬ ተከስተ አልቀረቡም ከተባለ በኋላ ጠበቃ ደምሴ ቀረቡ

የሰበር ተጠሪ፡- አቶ ከማል ሁሴን አልቀረቡም ተወካይ አዳሙ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የአፈጻጸም ክርክር ሲሆን የተጀመረዉ በስር ጅማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡ በስር ወረዳ ፍርድ ቤት የሰበር አመልካች የአፈጻጸም ከሳሽ የሰበር ተጠሪዉ የአፈጻጸም ተከሳሽ ነበሩ የሰበር ተጠሪዉ ስፋቱ 1.6 ሜትር የሆነ እና ቁመቱ 33 ሜትር የሆነ የመሬት ይዞታ የሰበር አመልካችን ድንበር አልፎ ካርታ በማሰራት ያካሄደዉን ግንባታ አፍርሶ ለሰበር አመልካች እንዲያስረክብ ተፈርዶበታል ፡፡

የሰበር አመልካች በዚሁ መሰረት እንዲፈጸምላቸዉ የአፈጻጸም ክስ በጅማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በሰበር ተጠሪዉ ላይ መሰርተዋል ፡፡ ጉዳዩ ቀረበለት የጅማ ወረዳ ፍርድ ቤት በፍርዱ መሰረት አፈጻጸም ተከሳሽ መሬቱን ቤትም ሆነ አጥር ገንብቶበት ከሆነ አፍርሶ የአፈጻጸም ከሳሽ የተፈረደላቸዉን 1.6 ሜትር በ33 ሜትር ይዞታ ሊያስረክብ ይገባል በማለት ትእዛዝ ተጥቷል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍር ድ አፈጻጸምዓላማአየገለግልም፣

በዚህ ትእዛዝ ያልተስማሙት የአሁን የሰበር ተጠሪ ቅሬታቸዉን በይግባኝ ለጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዉ የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 50148 እና 28019 ላይ ግልጽ ዉሳኔ ያላረፈበት ጉዳይ ሊፈጸም እንደማይችል አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ አሁን በተያዘዉ ጉዳይ የሰበር ተጠሪ 1.6 ሜትር በ33 ሜትር ላይ አጥር የሰራ መሆኑ እንጅ ቤት መስራቱ በፍርድ ልተረጋገጠ ስለሆነ አሁን ደግሞ ይዞታዉ ቤት ተሰርቶበታል ስለተባለ ቤት አፍርሶ ይዞታ ያስረክብ ማለት ከዋናዉ ዉሰኔ ያፈነገጠ ስለሆነ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ተገቢነት ያለዉ አይደለም በማለት ሽሮ መልስ ሰጭ ይዛዉ ከምትገኘዉ 878 ካሬ ሜትር ይዞታ ዉስጥ 1.6 ሜትር በ33 ሜትር ርዝመት የሰበር ተጠሪ ወሰን አልፎ የሰራዉን አጥር በማስፈረስ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ሊያስፈጽም ይገባል በማለት ጉዳዩን ወደ ስር ፍርድ ቤት መልሷል፡፡

የአሁን የሰበር አመልካች በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ቅሬታዋን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርባ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ የከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ስህተት የለበትም በማለት በማጽናት ዉሳኔ ሰጥቷል ፡፡

ቅሬታዉ ቀጥሎ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦም ሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰር ፍርድ ቤት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አልተፈጸም በማለት ቅሬታዉን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ሰርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ላይ ሲሆን አጭር ይዘቱ ዉሳኔዉ ሲሰጥ የሰበር ተጠሪ ቤቱን ይነካል ብለዉ አልተከራከሩም ፡፡ ስለዚህ 1.6 ሜትር በ33 ሜትር ይዞታ የሰበር አመልካችን ህጋዊ ይዞታ መያዙ ተረጋግጦ እንዲለቅ አስከተወሰነበት ድረስ ቤትም ይሁን አጥር አፍርሶ የማያስረክብበት ህጋዊ ምክንያት የለም ፡፡ በመሆኑም የወረዳዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ተገቢ ሆኖ ሳለ በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ዉሳኔዉ መሻሩ ስህተት ስለሆነ መታረም የሚገባዉ ነዉ የሚል ይዘት ያለዉ ነዉ ፡፡

ሰበር አጣሪ ችሎቱ ቅሬታዉን መርምሮ የሰበር አመልካች 1.6 ሜትር ቦታ ታልፎባቸዋል ተብሎ እንዲለቀቅላቸዉ አስከተወሰነ ድረስ ቤት አለበት ተብሎ ፍርዱ ሳይፈጸም የመቅረቱን ተገቢነት ተጠሪዉ ባለበት ለማጣራት ያስቀርባል ብሎ ግራ ቀኙ ክርክር አድርገዉበታል ፡፡

ተጠሪዉ ቀርቦ በሰጠዉ መልስ በወረዳዉ ፍርድ ቤት እንዲፈርስ የተባለዉ ቤት ከተሰራ ከአርባ አምስት አመት በላይ የሆነዉ ቪላ ቤት ነዉ ፤በዋናዉ ፍርድ የተሰጠዉ ዉሳኔ አጥር አፍርሶ ይልቀቅ የሚል ነዉ ፡፡ ስለዚህ የአፈጻጸም ዉሳኔዉ የተፈረደዉን ፍርድ ያገናዘበ አይደለም፡፡ አጥር

አፍርሶ ያስረክብ ተብሎ ተወስኖ ቤት አፍርሶ ያስረክብ ማለት ከዉሳኔዉ ያፈነገጠ አፈጻጸም ነዉ፡፡ ይህም ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/ 152172 በተመሳሳይ ጉዳይ የሰጠዉን አስገዳጅ ዉሳኔን የሚቃረን ነዉ፡፡ ስለዚህ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ተሸሮ አጥር አፍርሶ ያስረክብ ተብሎ መወሰኑ ተገቢነት ያለዉ ስለሆነ መጽናት የሚገባዉ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

የሰበር አመልካችም የሰበር አቤቱታቸዉን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበዉ ክርክሩ ተጠቃሏል፡፡ የክርክሩ አመጣጥ እና ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን እኛም ቅሬታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ በስር ፍርድ ቤት ከተደረገዉ ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እንዲሁም አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል ፡፡ እንደመረመርነዉም ቅሬታዉ ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ የሰበር አመልካች 1.6 ሜትር በ33 ሜትር ይዞታ ታልፎባቸዋል ተብሎ እንዲለቀቅላቸዉ አስከተወሰነ ድረስ ቤት አለበት ተብሎ ፍርዱ ሳይፈጸም የመቅረቱን ተገቢነት መልሰ ሰጪዉ ባለበት ለማጣራት ተብሎ በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምረናል ፡፡ እንደመረመርነዉም በዋናዉ ፍርድ የተሰጠዉ ወሳኔ የሰበር ተጠሪዉ ወደ ሰበር አመልካች ይዞታ አልፎ በያዘዉ1.6ሜትር በ33 ሜትር ይዞታ ላይ ያካሄደዉን ግንባታ አፍርሶ ለሰበር አመልካች ሊያሥረክብ ይገባል የሚል እንደሆነ ከፍርዱ መገንዘብ የሚቻል ነዉ ፡፡ የአፈጻጸም ችሎት በዚሁ ፍርድ አግባብ ከማስፈጸም ዉጭ ፍርዱን መቀነስም ይሁን መጨመር ወይም መሻሻል አይችልም ፡፡ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 28019፤152172፤50148 እና በሌሎች በርካታ የአፈጻጸም መዛግብት የሰጣቸዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉሞችም ይህንኑ የሚያረገግጡ ናቸዉ ፡፡የሰበር ተጠሪ ፍርዱ ግልጽ አይደለም ግልጽ ባልሆነበት ሁኔታ ሊፈጸም አይችልም አጥር እንጅ ቤት ይፍረስ የሚል ፍርድ አልተሰጠም በማለት አጥበቆ የሚከራከር መሆኑን እና ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ በሰ/መ/ቁ/ 152172 የሰጠዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉምም የሚቃረን ነዉ በማለት መከራከሩን ተመልክተናል ይሁን እና በፍርዱ የሰበር ተጠሪ ወደ ሰበር አመልካች ይዞታ 1.6 ሜትር በ33 ሜትር ተላልፎ ሰርቷል በተባለበት አቅጣጫ የተገነባዉ ግንባታ አጥርም ይሁን ቤት አፍርሶ ማስረከብ ያለበት መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ስለሆነ እና ከላይ ከተመለከትናቸዉ የሰበር ዉሳኔዎችም ሆነ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 378 እና 372 ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለዉ ፍርድ ሳይሸራረፍ መፈጸም ያለበት መሆኑን ስለሆነ ፍርዱ ግልጽ አይደለም የሚለዉ የተጠሪዉ ክርክር ተቀባይነት ያለዉ አይደለም ፡፡ ስለሆነም የስር የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፤ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ግልጽ ላልሆነ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ግልጽ ለሆነዉ አሁን ለያዝነዉ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለዉ ነዉ ብለዉ ዋቢ በማድረግ አጥር እንጅ ቤት ሊፈርስ አይገባም በማለት የወረዳዉ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ መሻራቸዉ በዋናዉ ፍርድ የተሰጠዉን ዉሳኔ ያልተከተለ እና መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ የተገኘ ነዉ ።

በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል

ዉሳኔ

የጅማ ዞን ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 61966 ሚያዚያ 12 ቀን 2014 ዓ/ም የጅማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር የሰጠዉ ዉሳኔ ፤ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባን ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 388094 ጥቅምት 01 ቀን 2015 ዓ/ም እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 406598 ህዳር 07 ቀን 2015 ዓ/ም ይንኑ ዉሳኔ በማጽናት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል።

የጅማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በአፈጻጸም መ/ቁ 61966 ሚያዚያ 12 ቀን 214 ዓ/ም የሰጠዉን የአፈጻጸም ዉሳኔ ተገቢ ነዉ ተብሎ ጸንቷል ።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ተ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍር ድ አ ፈ ጻ ጸ ም ዓ ላ ማአ የ ግ ለ ግ ል ም፣